# ትኋንን እናሸንፍ!

## ስለ ትኋኖች መሰረታዊ ነገሮች

- ትኋኖች ትናንሽ ነፍሳት ናቸው፣ የአፕል ፍሬ ያክላሉ። ያደጉ ትኋኖች፣ ጠፍጣፋ፣ ክብና የቀይ-ቡናማ ከለር አላቸው። ወጣት ትኋኖች በጣም ትንሽና ለማየት በጣም አስቸጋሪ ናቸው።

- ትኋኖች የሰዎችን ደም የሚመገቡ ሲሆን፣ ያለ ምንም ምግብ ለአንድ ዓመት ሊቆዩ ይችላሉ።

- ትኋኖች አብዛኛውን ግዜ ቀን ላይ ሰዎች በሚያርፉበት ወይም በሚተኙበት አካባቢ ይደበቁና ማታ ለመመገብ ይወጣሉ። ትኋኖች ሰውነታችን ላይ አይኖሩም።

- አንዳንድ ሰዎች በትኋን ሲነከሱ፣ ምንም አጸፋ እርምጃ አይወስዱም።

- አብዛኛዎቹ ትኋኖች ከአንድ ሰው የማረፊያ ቦታ በ 8 ጫማ ርቀት ውስጥ ይገኛሉ። በትኋን መወረሩ እየባሰ ሲሄድ፣ ትኋኖቹ እየተስፋፉ ይሄዳሉ። ትኋኖችን ከሚከተሉት ቦታዎች ውስጥ፣ በማንኛውም ቦታ ላይ ሊያገኟቸው ይችላሉ፥
  - በፍራሽ ውስጥ፣ በአልጋ ስፕሪንግ፣ በአልጋ መቃንና የአልጋ ንጣፎች ላይ
  - በቤት ቁሳቁስ ስንጣቂዎችና ክፍተቶች ውስጥ
  - በግድግዳ ወረቀት ልጣጭ ጀርባ
  - በፎቶዎችና ሰዓቶች ጀርባ
  - መጋረጃ ላይ
  - በእንጨት ወለል ክፍተቶች ውስጥ
  - በወለል ምንጣፎች ስር
  - በኤሌክትሪክ ሶኬቶች ወይም ማብሪያና ማጥፊያ ጀርባ

***ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ለትኋን የመረጃ መስመር በ 612-624-2200፣ 1-855-644-2200 ይደውሉ፣ bedbugs@umn.edu ይጻፉ፣ ወይም የ www.bedbugs.umn.edu ድረ ገጽ መጎብኘት ይችላሉ***

# በመኖሪያ ቤት ውስጥ ትኋኖችን መቆጣጠር

በቤትዎ ውስጥ ትኋንን ለመቆጣተር ሲሞክሩ፥

- በጓሮ አታክልቶች ወይም በእርሻ ላይ የሚያገለግሉ ጸረ ተባዮችን ***አይጠቀሙ***።
- “እቤት ውስጥ የተሰሩ” ወይም “በልዩ መንገድ የተሰሩ” የሚመስሉ ወይም የንግድ ፈቃድ ከሌለው ሰው የተገዙ ምርቶችን ***አይጠቀሙ***።

ትኋኖችን እቤዎት ውስጥ የሚቆጣጠሩበት የበለጠው መንገድ፣ ኬሚካላዊ እርምጃዎችንና በተባይ ተቆጣጣሪ ባለሙያ (PMP) የሚደረጉ በሙቀትተ ማስወገጃ እርምጃዎችን በማቀናበር ነው። ቢሆንም በ PMP የሚሰጥ አገልግሎት ውድ ሊሆን ይችላል። በዚህም ምክንያት፣ የትኋንን ወረራ እንዴት አድርገው እራስዎ መቆጣጠር እንደሚችሉ የሚገልጽ መረጃ እየሰጥዎ ነው።

ብቻዎን ትኋንን ለመቆጣጠር በጣም ከባድና ግዜ የሚወስድ ነው። ወንበርና ጠረጴዛዎችን፣ የቤት ቁሳቁሶችንና የግል እቃዎችን ማዘዋወር ያስፈልጋል። እያንዳንዱን ክፍል እንዴት አድርገው ማዘጋጀት እንደሚፈልጉ እቅድ ያውጡ። “ንጹህ የሆነ አካባቢ” ያዘጋጁ።

***“ንጹህ አካባቢ” እንዴት መፍጠር እንደሚቻል?***

- ✓ በአንድ ክፍት ገድግዳ ላይ ካሉ ማዕዘኖችና ጫፎች ይጀምሩ፣ የፕላስቲክ ካርድ ተጠቅመው ከስንጣቂዎችና ክፍተቶች ውስጥ ነገሮችን ቆፍረው ያውጡ።
- ✓ እግረ መንገድዎን ስንጣቂዎቹና ክፍተቶቹን ሁሉ እየመረመሩ ይሂዱ
- ✓ ታይል ወይም እንጨት ወለል ካልዎት፣ እርጥብ ጨርቅ ወይም መወልወያ ተጠቅመው መወልወል ይችላሉ፣ ካልሆነ ግን ሁሉንም ቦታ በደምብ ቫክዩም ያድርጉ
- ✓ ፎቶዎችንና ሌሎች በግድግዳ ላይ የተንጠለጠሉ ነገሮችን ማጽዳቱን አይርሱ
- ✓ ሌሎች እቃዎችን መርምረው በንጹህ አካባቢ ውስጥ ያስቀምጧቸው
- ✓ ልብሶችን፣ የአልጋ ማንጠፊያዎችንና ሌሎች ሊታጠቡ የሚችሉ ነገሮችን አንድ በአንድ መርጠው ያዘጋጁ፣ ይህ የተወረሩ ከትኋን ነጻ ለማድረግ በጣም የተሻለው መንገድ ነው።
- ✓ ንጹህ የሆነ አካባቢ ለማዘጋጀት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በ http://www.bedbugs.umn.edu/bed-bug-control-in-residences/controlling-bed-bugs-by-hand/ ድረ ገጽ ይመልከቱ።

**ትኋኖችን በእጅ መግደል** 100 በመቶ ስኬታማ የሆነ አይደለም፣ ቢሆንም እቤትዎ ውስጥ የትኋኖችን ቁጥር እንዲቀንሱ ይረዳዎታል። ይዘው መጨፍለቅ ወይም በሚያጣብቅ ፕላስተር አጣብቆ በመያዝ ፕላስተሩን መጣል ይችላሉ።




*ትኋኖችን ኢድኖ ለመያዝና ለመደምሰስ የሚያስችሉ መገልገያዎች፥* የእጅ ባትሪ፣ ያረጀ ክሬዲት ካርድ (ወይም ተመሳሳይ) እንደ መስተዋት የሚያሳይ ፕላስተር፣ የላስቲክ ኮሮጆ፣ ጨርቅና ሙቅ ሳሙና የተቀላቀለበት ውሃ።

*ቅደም ተከተሎች፥* የእጅ ባትሪና ክሬዲት ካርድ ተጠቅመው፣ ክሬዲት ካርዱን በስንጣቂዎችና ክፍተቶች ውስጥ በማንሸራተት ትኋኖች እንዳሉት ማየት ይችላሉ። በሚያጣብቅ ፕላስተር ትኋኖችን ለመያዝ ይጠቀሙበት። ይህን ሞቅ ያለ ሳሙና የተቀላቀለበትን ውሃ የተወረረውን ቦታ፣ ትኋኖቹን፣ የደም ጠብታዎችን፣ ዓይነምድሩን፣ እንቁላሉንና የቆዳ ቅራፊዎችን ለማጠብ ይጠቀሙበት።

**ቫክዩም ማድረግ** ትኋኖችን ቶሎ ይዞ ለመቆጣጠር ይረዳል። በመጋረጃ ሳንቃዎች፣ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች (እንደ ቴሌቪዥንና ስቴሪዮ የመሳሰሉ) እና እንደ አልጋ፣ ሳሎን፣ ሶፋዎች፣ የአልጋ መቃኖችና የልብስ ሳጥኖች በመሳሰሉት መደበቂያ ሊሆኑ በሚችሉት አካባቢዎች ቫክዩም ያድርጉ። የማጠራቀምያ ጣሳ ያለው ቫክዩም የሚጠቀሙ ከሆኑ፣ የተጠራቀመውን ወዲያዉኑ ወደ ፕላስቲክ ኮሮጆ ይጨምሩና፣ አሽገው ይጣሉ። ቫክዩሙን በደምብ አድርገው ያጽዱ። የላስቲክ ኮሮጆ የተጣበቀበት ቫክዩም የሚጠቀሙ ከሆኑ፣ ኮሮጆውን ወዲያው ያውልቁና በላስቲክ ውስጥ አሽገው ይጣሉ። ቫክዩሙ ውስጥ ምንም የቀሩ ትኋኖች እንዳይኖሩ ይፈትሹና፣ ትኋኖቹ ወደ ሌላ ቦታ እንዳይስፋፉ ለመግታት ትኋኖቹን ይግደሏቸው።

Amharic Translation Date: September 2015

# ትኋንን እናሸንፍ!

**ማጠብ**፣ በልብስ ማጠቢያ ማሽንና ማድረቅያ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ነገሮችን ከትኋን ነጻ ለማድረግ በጣም ፍቱን የማጽጃ መንገድ ነው። ጨርቆችንና የቆሸሹ ልብሶችን ሰብስበው እስከሚታጠቡበት ግዜ ድረስ በላስቲክ አሽገው በማቆየት ትኋን የሚሰራጭበትን ዕድል መቀነስ ይችላሉ። በሚያጥቡበትና በሚያደርቁበት ወቅት፣ ጨርቁ ሊቋቋመው የሚችል ከፍተኛውን የሚቀት መጠን ይጠቀሙ። አንድ እቃ ሊታጠብ የሚችል ካልሆነ፣ እቃው ሊቋቋመው በሚችለው ከፍተኛው የሙቀት መጠን ለ 30 ደቂቃ ያድርቁ።



**እንፋሎት**፣ በትክክል ከተደረገ ስኬታማ ሊሆን ይችላል። 1 ጋሎን መጠን ያለው፣ ቢቻል የመጠን መቆጣጠሪያ ያለው፣ ለንግድ አገልግሎት በሚሆን እንፋሎት ማመንጫ ይጠቀሙ። የወለል ወይም የሶፋ ልብስ መግጠሚያዎች የቤት እቃዎቹ ጨርቅ ወይም መሸፈኛ ውስጥ እንፋሎት ዘልቆ እንዲገባ ያደርጋል። ትኋኖችን ጨርሶ ለመግደል፣ ልክ የእንፋሎቱ መጥረጊያ በእቃው አካል ላይ ካለፈ በኋላ የሙቀቱ መጠን ከ 160-180°F መሆን ይኖርበታል። የሙቀቱን መጠን ለመለካት፣ የኢንፍራሬድ ቴርሞሜትር ይጠቀሙ። ጥንቃቄ ያድርጉ ምክንያቱም እንፋሎት ሊያቃጥልዎ ይችላል።

በትኋን የተወረሩ እቃዎችን **ማቀዝቀዝ**፣ ትኋንን ለመግደል ቀላሉ መንገድ ነው። ፍሪዘርና ግዜ ብቻ ነው የሚያስፈልግዎ። ትኋንን ለመግደል እቃዎችን ለማቀዝቀዝ፣ እቃዎቹን ቢያንስ ለ 4 ቀኖች፣ በ 0°F ወይም ከዚያ በታች በሆነ የሙቀት ደረጃ ማቀዝቀዝ ይኖርብዎታል። ማቀዝቀዝ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል፣ ምን ነገር እንደሚያቀዘቅዙ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልግዎታል።



**የፍራሽ ማሸጊያ ጨርቆች**፣ ትኋኖች በፍራሹ ውስጥ ገብተው እንዳይደበቁ ያግዳቸዋል፣ ፍራሽ ዋናው ትኋኖች የሚገኙበት ቦታ ሲሆን እሱን ከትኋን ነጻ ማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው። አንድ ፍራሽ በትኋን ከተወረረ፣ ወረራውን ለመቆጣጠር በማሸጊያ ጨርቅ ይሸፍኑት፣ ትኋኖቹም ከ 2 ሳምንት በኋላ መሞት ይጀምራሉ፣ ቢሆንም ቢያንስ ለ 18 ወራት ሸፍነው ያቆዩት። በተጨማሪም፣ አዲስ የትኋን ወረራ ቢከሰት፣ የፍራሽ መሸፈኛዎችን ለማጽዳት በጣም ቀላል ነው። ትኋንን ለመከላከል ተብለው የተሰሩ የፍራሽ መሸፈኛዎችን ብቻ ይግዙ፣ የአለርጂ መንስኤዎችን ለመከላከል ተብለው የተሰሩ የአልጋ ሸፋኖች ትኋንን መከላከል ላይችሉ ይችላሉ።

**ደረቅ ሙቀት መጠቀሙ** ትኋኖችን የመከላከያ ስኬታማ መንገድ ነው። የተበከሉት እቃዎችና ክፍሎች፣ ተባዩን ለመግደል በሚያስችል ተገቢው የሙቀት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል ይህ የማጽጃ መንገድ መደረግ ያለበት በተባይ መቆጣጠሪያ ባለሞያ (Pest Management Professional) ብቻ ነው። እራስዎ ብቻዎን ይህን የሙቀት አጠቃቀም መንገድ አይሞክሩ።

**ጸረ ባይ መድሃኒቶች** ትኋንን ለመቆጣጠር በጣም አስፈላጊ ሚና ይጫወታሉ፣ ትኋኖች በተናጠል መድሃኒት የሚረጭበትን ቦታ ትተው ወደ ሌላ ቦታ መሸሽ ልማዳቸው ስለሆነ። የጸረ ተባይ መድሃኒቶችን ሁሉ በጽሁፍ ምልክቱ መሰረት በጥንቃቄ ይጠቀሙ። ተገቢውን የጸረ ተባይ መድሃኒት ለመጠቀም፣ የተባይ መቆጣጠሪያ ባለሞያ መቅጠሩ በጣም አስፈላ ነው። ለሌሎች ተባዮች ተብሎ በጽሁፍ ምልክቱ ላይ የተገለጸ መድሃኒትን በትኋኖች ላይ አይጠቀሙ፣ ይህንን ካደረጉ ትኋኖቹ ይበታተኑና የሚበክሉትን ቦታ ያሰፋዋል።

**ስለነዚህ እያንዳንዳቸው መንገዶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ www.bedbugs.umn.edu ድረ ገጽን ይጎብኙ**

Amharic Translation Date: September 2015

መስከረም 29, 2014 ላይ ተሻሻለ

በ Amelia Shindelar እና Dr. Stephen Kells፣ 2011

ለ "ትኋንን እናሸንፍ" ዘምቻ የገንዘብ ድጎማ የተሰጠው በ United States Environmental Protection Agency እና MDA ነው። ከ Minnesota Department of Health ስለተገኘው ተጨማሪ እርዳታ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

በ Americans with Disabilities Act አዋጅ መሰረት፣ ይህን መረጃ በተለያየ የመገናኛ መልክ በ 651/201-6000 ደውሎ ማግኘት ይቻላል። የ TTY ተጠቃሚዎች ለ Minnesota Relay Service በ 711 ወይም 1-800-627-3529 መደወል ይችላሉ። የ University of Minnesota እና MDA ለሁሉም እኩል ዕድል የሚሰጡ አስተማሪዎችና አሰሪዎች ናቸው።

MINNESOTA DEPARTMENT OF AGRICULTURE www.mda.state.mn.us

UNIVERSITY OF MINNESOTA EXTENSION